# ካርባፒነም - ተቋቋሚ ኤንተሮባክቴርያሴ (CRE)

## ካርባፒነም - ተቋቋሚ ኤንተሮባክቴርያሴ (CRE) ምንድነው?

ኤንተሮባክቴያሴ በሰዎች የምግብ መተላለፊያ ውስጥ የሚገኙ የባክቴርያ ስብስብ ናቸው። የተለመዱት አይነቶች *ኢ ኮሊ* እና *ክሌብሴላ* ዝርያዎችን ያካትታሉ። ካርባፔኔሞች ሌሎች መድሃኒቶችን የሚቋቋሙ ባክቴርያዎችን ለማከም ጥቅም ላይ የሚውሉ የፀረ-ተሕዋስያን ምድቦች ናቸው። እነዚህ ፀረ-ተሕዋስያን ከልክ በላይ አገልግሎት ላይ በመዋላቸው፣ የኤንተሮባክተሪያሴ የተወሰኑ አይነቶች ከርባፔኔሞችን ይቋቋማሉ እንዲሁም እነዚህ ባክቴርያዎች ካርባፒነም - ተቋቋሚ ኤንተሮባክቴርያሴ (CRE) በመባል ይታወቃሉ።

## CRE የሚዘው ማንን ነው?

ጤናማ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የCRE ኢንፌክሽን አያጋጥማቸውም። በጤና ክብካቤ ቦታዎች፣ የCRE ኢንፌክሽን ለሌሎች ሕመሞች ሕክምና እየተሰጣቸው ያሉ ታካሚዎች ላይ ሊከሰት ይችላል። እንደ መተንፈሻ መሳሪያ፣ የሽንት ካቴተሮች፣ ወይም የውስጠ ደም-መልስ ካቴተሮች፣ እንዲሁም ለረጅም ጊዜ የተወሰኑ ፀረ-ተሕዋስያን መድሃኒት የሚወስዱ ሰዎች ከፍተኛ በCRE የመያዝ ስጋት አለባቸው።

## CRE የሚዛመተው እንዴት ነው?

CRE ከታማሚው ሰው ጋር በሚኖር የቀጥታ ንክኪ ወይም የተበከሉ ዕቃዎችን (ለምሳሌ፣ የሕክምና መሳሪያ) ወይም አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን (ለምሳሌ የአልጋ መደገፊያ ወይም የበር እጀታዎችን) በመንካት ደግሞ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሊተላለፍ ይችላል።

## የCRE ሕመም ምልክቶች ምንድናቸው?

አንዳንድ ሰዎች ምንም የሕመም ምልክት ሳያሳዩ CRE ባክቴርያን በሰውነታቸው ውስጥ ይሸከማሉ። ይህ "መያዝ" ይባላል። አንድ ሰው ተይዞ ለረጅም ጊዜ ወይም መቼም ቢሆን ሳይታመም ሊቆይ ይችላል። ኤንተሮባችተሪያሴ የአንጀት እና የምግብ መተላለፊያ፣ የሳንባ ምች፣ የቁስል ኢንፌክሽኖችን፣ የደም እና ሌሎች የሰውነት አካላት ወራሪ ኢንፌክኖችን ጨምሮ የተለያዩ ኢንፌክሽኖችን ሊያስከትል ይችላል። CRE ተመሳሳይ ኢንፌክሽኖችን ያስከትላሉ፣ ይሁን እንጂ ኢንፌክሽኖቹ ለማከም ከባድ ናቸው።

## የበሽታው ምልክቶች፣ ለበሽታው ከተጋለጡ ከስንት ጊዜ በኋላ ይታያሉ?

ለበሽታው ከተጋለጡ በኋላ የሕመሙ ምልክቶች ከመታየታቸው በፊት ምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ለCRE ለበሽታው ከተጋለጡ በኃላ የሕመሙ ምልክቶች በምን ያህል ጊዜ እንደሚታዩ በደንብ አይታወቅም። በአብዛኞቹ ሁኔታዎች፣ ለCRE መጋለጥ ወደ ሕመም አያመራም። አንድ ሰው CRE በሰውነቱ ውስጥ ቢሸከምም የሕመም ምልክቶችን ላያሳይ ይችላል፣ ወይም በCRE ምክንያት ከቀናት ወይም ሳምንታት በኋላ ሊታመም ይችላል።

## CRE በምርመራ የሚገኘው እንዴት ነው?

ኢንፌክሽኖችን የሚያስከትሉ የተወሰኑ ባክቴርያዎችን እና የትኛው ፀረ-ተሕዋስያን ኢንፌክሽኖቹን ለማከም ውጤታማ እንደሚሆን ለመለየት ልዩ ምርመራዎች ያስፈልጋሉ።

## የCRE ሕክምና ምንድነው?

የሕክምና አማራጮች እንደየ የCRE ኢንፌክሽኑ አይነት ይለያያሉ። ባክቴርያው የተወሰኑ የፀረ-ተሕዋስያን አይነቶችን መቋቋም ካልጀመረ በስተቀር አንዳንድ CRE ኢንፌክሽኖች መታከም ይችላሉ። አንዳንድ CRE "ሁሉን ተቋቋሚ" ናቸው፤ ይኸም ማለት የCRE ባክቴርያው ሁሉንም የተሞከሩ ፀረ-ተሕዋስያን መድሃኒቶች ይቋቋማል ማለት ነው። በCRE ከተያዙ ሐኪምዎ ተመራጩን የሕክምና ሂደት ለመምረጥ ከእርስዎ ጋር ይሰራል።

## የCREን ስርጭት እንዴት መግታት ይቻላል?

የተወሰኑ የኢንፌክሽን መከላከያ ልማዶች (ለምሳሌ CRE ያለባቸውን ሰዎች በሚያክሙ ጊዜ ጋውን እና ጓንት ማጥለቅ፣ እንዲሁም በተደጋጋሚ እጅን መታጠብ) በጤና አገልግሎት መስጫ በታዎች ውስጥ የCREን ስርጭት ሊገድብ ይችላል። CRE ያለባቸው ታካሚዎች በጤና አገልግሎት አቅራቢያቸው የሚነገሯቸውን መመሪያዎች መከተል እና፤ የተበከለውን አካባቢ ከነኩ ወይም ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ የእጃቸውን ንጽሕና መጠበቅ አለባቸው።

በሆስፒታል የተኛን የCRE ታካሚ የሚጎበኙ ጓደኞች ወይም የቤተሰብ አባላት፣ በሆስፒታል የሚሰጡትን ማስጠንቀቂያዎች ማክበርና መከተል አለባቸው። የጤና ክብካቤ ተቋማት በበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (CDC) CRE የመሳሪያ ጥቅል ውስጥ የተቀመጡ መመሪያዎችን መከተል ይችላሉ (https://www.cdc.gov/hai/organisms/cre/cre-toolkit/index.html)።

## CRE ቢኖርብኝስ?

ወደ ሕክምና ቀጠሮ፣ ሆስፒታል፣ የአረጋውያን መንከባከቢያ ማዕከል፣ ወይም የኩላሊት እጥበት ማዕከል በሚሄዱ ጊዜ፣ ለጤና አገልግሎት አቅራቢው መንገርዎን አይዘንጉ። የባክቴርያውን ስም ለማስታወስ እገዛ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ይህን ወረቀት ይዘው ይሂዱ።

የጤና ክብካቤ አቅራቢዎን መመሪያዎች ይከተሉ። አቅራቢዎ ፀረ-ተሕዋስያን መድሃኒት ካዘዘልዎ፣ ልክ እንደታዘዘው ይውሰዱ እንዲሁም፣ ቢሻልዎም እንኳን ሙሉውን መጠን ወስደው ይጨርሱ። አቅራቢዎ የሚሰጥዎትን ሌሎች የሕክምና እና የንጽሕና ምክሮች በሙሉ ይከተሉ።

እጅዎን በሳሙና እና ለብ ባለ ውሃ ይታጠቡ፣ በተለይም ምግብ ከመመገብዎ ወይም ከማዘጋጀትዎ በፊት፣ የቁስል ሽፋኖችን ወይም ባንዴጆችን ከመቀየርዎ በፊት እና በኋላ፣ ሽንት ቤት ከተጠቀሙ በኋላ፣ እንዲሁም አፍንጫዎን ከተናፈጡ፣ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ በኋላ። ውሃ እና ሳሙና በማይገኝ ጊዜ ከአልኮል የተሰራ የእጅ ንጽሕና መጠበቂያ ይጠቀሙ። ይህ ለሁሉም ሰው መልካም ምክር ነው። አገልግሎት አቅራቢዎች ለእርስዎ እንክብካቤ ከማቅረባቸው በፊት እጃቸውን መታጠባቸውን ያረጋግጡ። እነርሱም ቁስል ከነኩ፣ ሽንት ቤት እንዲጠቀሙ ከረዱዎ እና ሰገራ ካጸዱ በኋላ፤ እንዲሁም የሕክምና መሳሪያዎችን ከመያዛቸው በፊት እና ከያዙ በኋላ (ለምሳሌ የሽንት ካቲተሮችን) እጃቸውን መታጠብ አለባቸው። ከሰውነት ፈሳሾች ወይም ደም ጋር ንክኪ ሊፈጠር ስለሚችል ጓንቶች አገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው።

## በቤት ውስጥ CRE ላለበት ሰው እንክብካቤ የማቀርብ ከሆነስ?

CRE ብዙውን ጊዜ ችግር የሚሆነው ከበስተጀርባ ሌላ የጤና እክል ላለባቸው ሰዎች፤ በተለይም እንደ የሽንት ካቲተር ወይም የቆዩ ቁስሎች ላሉባቸው ሰዎች ነው። ያ ካልሆነ፣ ጤናማ ሰዎች ከCRE በሚመጡ ችግሮች ለመያዝ ያላቸው ስጋት በአንጻራዊነት ዝቅተኛ ነው።

CRE ላለባቸው ሰዎች እንክብካቤ የሚያቀርቡ ሰዎች እጃቸውን ከመታጠብ አንጻር ጥንቁቅ መሆን አለባቸው፣ በተለይ ቁስል ከነኩ ወይም የCRE ሕመምተኛው ሽንት ቤት እንዲጠቀም ከረዱ ወይም ሰገራ ካጸዱ በኋላ። እንክብካቤ አቅራቢዎች የታካሚውን የሕክምና መሳሪያዎች (ለምሳሌ የሽንት ካቲተር) ከመንካታቸው በፊት እና ከነኩ በኋላ እጃቸውን መታጠብ መዘንጋት የለባቸውም። ይህ በተለይ አስፈላጊ የሚሆነው እንክብካቤ አቅራቢው ከአንድ በላይ ለሆነ ሕመምተኛ እንክብካቤ የሚያቀርብ ከሆነ ነው። በተጨማሪም ከሰውነት ፈሳሾች ወይም ደም ጋር ንክኪ ሊፈጠር እንደሚችል የሚጠበቅ ከሆነ ጓንቶች አገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው።

## ስለ CRE የበለጠ መረጃ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

- CREን በተመለከተ ስጋቶች ካሉዎት፣ የጤና ክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።
- ለአካባቢዎ የጤና መምሪያ ይደውሉ። የአካባቢ ጤና መምሪያዎች ማውጫ እዚህ ይገኛል፦

  http://www.vdh.virginia.gov/local-health-districts/።
- በጤና ክብካቤ ተቋም ውስጥ የCRE አያያዝን በተመለከተ የቨርጂኒያ የጤና መምሪያ ድር ጣቢያን ይጎብኙ፦ http://www.vdh.virginia.gov/surveillance-and-investigation/hai/organisms/።
- የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል (Center for Disease Control and Prevention) ድር ጣቢያን ይጎብኙ፦https://www.cdc.gov/HAI/organisms/cre/ ።

ኦገስት 2018